ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ

Coalition for Unity and Democracy Party
(Kinijit)

http://www.kinijitethiopia.org
e-mail kil@kinijitinternational.org Voice Mail/Fax 1-206-203-3974

ጋዜጣዊ መግለጫ

ኪል-005/07
የከቲት 2 ቀን 1999 ዓ. ም.

# ለፍትህ ዘብ መቆም ታሪካዊ ግዴታ ነው

አገራችን ኢትዮጵያ በልጆችዋ የተባበረ አኩሪ አገራዊ ትግል በተከፈለ ታላቅ መስዋእትነት ተጠብቆ የኖረ ረጂም ጥንታዊ የመንግስትነት ታሪክ ቢኖራትም ይህንን አኩሪ የረጂም ዘመን ታሪክ በዲሞክራሲያዊ ሰርአት አጎልብቶ፣ የህግ የበላይነትን አስፍኖ፣ ዜጎችን ከአምባገነናዊ አገዛዝ ምርኮኛነት አላቆ ተጠሪነቱ ለኢትዮጵያ ህዝብ የሆነ መንግሰት ባለቤት መሆን ግን አልቻለችም::

በተከታታይ በትረ-ሥልጣኑን የተረከቡት አገዛዞች በጠብመንጃ የተረከቡዋትን ሥልጣን በጠብመንጃ ከመጠበቅ አልፈው የህዝባችንን የሥልጣን ምንጭነትና ባለቤትነት መቀበል አልተቻላቸውም:: ይህንን በመሰለ የአምባገነኖች የሥልጣን ቅብብሎሽ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሰላም አየርን ተነፍጎ ወልዶ በሚስምባትና ሰርቶ በሚከበርባት እናት አገሩ በስሙ በሚነግዱ ገዥዎች እየተረገጠ ይገኛል:: የዕነዚህን የጥፋት በትሮች የጭካኔ አገዛዝ እንዳይቀጥል ለማሰቻል የኢትዮጵያ ሕዝብ በቃኝ አሻፈረኝ ብሎ ተንቀሳቀሰ::

ይህ በቅንጂትና ለሌሎች ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ድርጅቶች  ግንባር ቀደም ተዋናይነት የተጀመረው የነጻነት እንቅስቃሴ በምርጫ 1997 ታሪካዊ ድልን አስመዘገበ:: ጠንካራ ተፎካካሪ የለብኝም ብሎ ይደነፋ የነበረው የወያኔ/ኢህአዴግ አገዛዝ በሕዝብ የድምጽ ማእበል ክፉኛ ተመታ:: ሕዝባችን የነጻነቱ ባለቤት ብቻ ሳይሆን የመንግስት ሥልጣንና ምንጭ ብቸኛ ሃይል ሊሆን እንደሚችል አረጋገጠ:: ኑሮየን ያሻሽልሉኛል፣ የተረጋጋ ህብረተሰባዊ ሰላምን ይፈጥሩልኛል፣ በልጆችዋ አንድነት  የተጠናከረችና በስልጣኔ የተራመደች ኢትዮጵያን ይገነባሉ፣ ብሎ ላመነባቸው የህዘብ ልጆች ታሪካዊ ድምጹን ሰጠ:: ቅንጂት ለአንድነትና ለዴሞከራሲ ፓርቲ በዚህ ታሪካዊ ወቅት ነበር ታላቅ ሕዝባዊ አመኔታና ወገናዊ ፍቅርን ተላብሶ ያዲሲትዋ ዴሞከራሲያዊት ኢትዮጵያ አደራ ተረካቢ ዕንዲሆን የተመረጠው::

የወያኔ/ኢህዴግ አገዛዝና የስልጣን መጠበቂያ ተቅዋሞች የቆሙበት የሥልጣን መሰረት መናጋቱን ለአመታት የገነቡት የጥላቻ ፖለቲካ መናዱን የኢትዮጵያ ህዝብ የግፈኞች አገዛዝ መሸከም የማይችልበት ደረጃ ላይ መሆኑን በመረዳት የነጻነት ትግሉን ለማኮላሸት ያለ የሌለ ሃይላቸውን አንቀሳቀሱ:: የለዉጥ ሃዋሪያ የሆኑትን የቅንጂት ለአንድነትና ለዴሞከራሲ ፓርቲ መሪዎችን፣ አባሎችን፣ ደጋፊዎችን፣ የሕዝብ አይንና ጆሮ ሆነው የህዝባቸውን የመረጃ ጥማት ለማርካት የተንቀሳቀሱትን የነፃውን ፕሬስ ህብረተሰብ አባላትንና የሲቪሉን ኅብረተሰብ አመራሮችን ሰብስበው በእስር በማጎር ተቃውሞዉን ያሰማውን ወገን ባደባባይ የረሸኑት:: የሕዝብን ተሰፋና የነጻነት ጥማት በመግደልና በማሰር ለጊዜው ያስቆሙት ሊመሰላቸው ይችላል:: ሕዘባችን የቅንጂት መሪዎቻችን ደጋግመው ዕንዳሉት የፍርሃት ስንሰለቱን በጣጥሶ ለመብቱና ለነጻነቱ ሊታገል የተነሳ ሕዝባዊ ሃይል እንጂ እነ መለስ ዜናዊ እንደሚሉት በጠብመንጃ የገነቡትን ዘረኛ አገዛዝ በሃይል ለመናድ አይደለም::

**ውድ የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ!**

የወያኔ/ኢህዴግ አገዛዝ ላለፉት አስራ አምስት ዓመታት የጫነብህን ዘረኛ አገዛዝ በሥልጣን ምንጭነትህና ባለቤትነትህ መብት ተጠቅመህ በድምጽህ በምርጫ ሳጥን ለመለወጥ ያደረግከው ታላቅ ጥረት ከሽፎ ከፍተኛ የደም ግብር እያስከፈለህ ይገኛል:: አንተም እንደማንኛውም የተቀረው የዓለም ህዝብ ለነጻነትህና ለመብትህ የሰጠህው ድምጽ እንጂ የፈጸምከው ወንጀል የለም:: ውድና የምትሳሳላቸው ብርቅዬ የቅንጂት መሪዎችህም ለዓመታት ያካበቱትን ልምድና ዕውቀት ብዕርና ዕርሳስ ጨብጠው የፖለቲካ አማራጭ አቀረቡልህ እንጂ ዘረኛ ገዥዎቻችን እንደሚሉት የዕልቂት ደመና አርግዘው የጥፋት ዝናም አላዘነቡም:: ለነጻነትህና ለመብትህ መከበር ብለው ካንተ በፊት እኛን ያድርገን አሉ እንጂ ቃላቸውን አጥፈው ለጥቅማጥቅም ተንበርክከው አላሳፈሩህም:: ዛሬ

የህዝብን ድምጽ የሰረቀው የወያኔ/ኢ.ህዴግ አገዛዝ ይባስ ብሎ ባሰርት ሺ.ዎች የሚቆጠሩ የህሊናና የፖለቲካ እስረኞች መሪዎቻችንን ጨምሮ ባገር ክህደት ከሶ በካድሬ ዳኞቹ የጥፋተኝነት ውሳኔ ለመስጠት በዝግጅት ላይ ይገኛል:: ይህንን የመሰለ አይን ያወጣ በደል እስከ መቼ በጸጋ ተቀብሎ መኖር ይቻላል::

ትናንት የወያኔ/ኢ.ህዴግ አገዛዝን አማራጭ የለሽ የፖለቲካ ስርአት በድምጽህ አሽቀንጥረህ ጥለሃል:: ይህ አገዛዝ መሪዎችህን አስሮ አንተን በመሳሪያ ሃይል አፍኖ የስልጣን ዕድሜውን ለማራዘም ደፋ ቀና ዕያለ ነው:: መንግስታዊ ሽብርን በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ጭነው የውጭ አሳዳሪዎቻቸው የጸረ ሽብርተኝነት ተዋናይ ለመምሰል በውድ ልጆችህ ደም ሲዳዳቸው ይሰተዋላል:: ይሄንን የመሰለ የግፈኞች አገዛዝ ዛሬ በቃህ ካልተባለ ኢትዮጵያችንም እንደ አገር ኢትዮጵያውያንም እንደ ህዝብ የመቀጠላችን ሁኔታ በጣም ያጠራጥራል:: ትናንት በድምጽህ የመረጥካቸውን መሪዎቻችንን፣ አንደበትህ ሆነው ያገለገሉ ህዝባዊ ጋዜጠኞችህንና የመብትህ ተሟጋቾችን በዘር ማጥፋት ወንጀል ከስው ከማሰቃየት አልፈው የካቲት 12/1999 ዓ.ም ውሳኔ ለመስጠት ዝግጅታቸውን መጨረሳቸውን የሚደርሱን መረጃዎች ይጠቁማሉ:: ይህንን ያምባገነኖች ፍርድ ዛሬ ማስቆም ካልቻልን ፍትህና ዴሞክራሲን ባገራችን ለማምጣት የታገልንለት ትግልም አብሮ ይጨፈለቃል:: ሥለዚህ ባገዛዙ ላይ ትርጉም ያለው ተጽዕኖ ለማሳደር የሚከተለውን ጥሪ ዕናቀርባለን::

ሀ. የክርስትና እምነት ተከታዮች በመላ ኢትዮጵያ ቤተክርስትያኖችና አድባራት በብዛት በመገኘት ለታሰሩትና ለተሰደዱት ተከታታይ ጸሎት እንድታደርጉ በትህትና እናሳስባለን፣ ይህ ሕዝባዊ የጸሎት ሥነሥርዓት እሁድ ከየከቲት 11 ቀን 1999 ዓ. ም. ጀምሮ ወያኔ/ኢ.ህአደግ ለሕዝብ ጥያቄ እስከሚገዛ ድርስ እንዲቀጥል እናስገነዝባለን::

ለ. የስልምና እምነት ተከታዮች በመላ ኢትዮጵያ በሚገኙ መሰጊዶችና ሌሎች ተመሳሣይ የጸሎት ቦታዎች በገፍ በመገኘት ተመሳሳይና ተከታታይ ጸሎቶች ዕንድታደርጉ በትህትና ዕኘጠይቃለን፣ ይህ ሕዝባዊ የጸሎት ሥነሥርዓት አርብ እለት ከየከቲት 9 ቀን 1999 ዓ. ም. ጀምሮ ወያኔ/ኢ.ህአደግ ለሕዝብ ጥያቄ እስከሚገዛ ድርስ እንዲቀጥል እናስገነዝባለን::

ሐ. መሪዎቻችን እስከሚፈቱ ድረስ በእረፍትና ከስራ ሰአት ውጭ የኢትዮጵያን ከተሞች ጭር በማድረግ እምቢተኝነታችንን እናሳይ:: ቀድም ብለው በቅንጂት የወጡ የሰላማዊ ትግል ዘዴዎችም በብርቱ ጥንቃቄና ዘዴ ሥራ ላይ እንዲውሉ አበክረን እናሳሰባለን::

**መ. ለኢትዮጵያ ወጣቶችና ተማሪዎች!**

እናንት የዛሬው ትውልድ ተረካቢ.ዎች፣ ገንቢ.ዎችና አስረካቢ.ዎች የሆናችሁ ወድ የኢትዮጵያ ልጆች ባገራችን አምባገነናዊ ሥርዓት አብቅቶ ዘመናዊ ዴሞክራሲ.ያዊ የፖለቲካ ሥርዓት እንዲገነባ የፈጸማችሁት ታሪካዊ ተጋድሎና የከፈላችሁት ታላቅ መሥዋዕትነት በአገራችን ታሪከ ለዘለዓለም ሲወሳ ይኖራል:: አገራችን ወደ ዴሞክራሲ.ያዊ ሥርዓት እንድትሸጋገር የነበራቸሁ ህልም ዛሬም ተጨናግፎ እንደትናንቱ የደም ግብር እያስከፈለ ይገኛል:: የታሰሩ መሪዎቻችን ዕንዲፈቱ ያነሳቻሁት ጥያቄ ዛሬም ሕያው ነው:: ይህ በታላቅ አገራዊ ቃልኪዳን የተጀመረው የለውጥ ጉዞ የፖለቲካና የህሊና ዕስረኞቻችን ተፈተው ሕዝባችን የመብቱና የነጻነቱ ባለቤት መሆን እስከሚችል ድረስ አጠናክሮ ከመቀጠል በሥተቀር ሌላ አማራጭ የለንም::

አሁን ልንከተለው የሚገባ የትግል ሥልት ደማችንን በከንቱ እንዲያፈሱ የተመቻቸ እድል የሚሰጥ መሆን አይገባውም:: ብርቱ ጥንቃቄ በተመላበት በየትምህርት ቤቱና ከፍተኛ ትምህርት ተቐማት ተጠናክረው የሚቀጥሉና መላውን ኢትዮጵያ በአንድ ወቅት የሚሸፍኑ መሆን አለባቸው::

ሀ. ስለዚህ ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ እስከ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ዉስጥ በትምህርት ገበታ ላይ ያላችሁ ኢትዮጵያዊያን ከሰኞ የከቲት 5 ቀን 1999 ዓ. ም. ጀምሮ ለአንድ ሳምንት እቤታችሁ እንድትቆዩ እናሳስባለን::

ለ. በዚህ በአንድ ሳምንት ጊዜ ዉስጥ መንግሥት ለሕዝብ ጥያቄ አዉንታዊ ምላሽ ከልሰጠ አድማዉን በመቀጠል ከቅንጅት የሚሰጡትን ተከታታይ መመሪያዎችን እንድትጠባበቁ እናስገነዝባለን::

ሐ. በትምህርት ማቆም በሚደረግበት ጊዜ ሰላማዊ ሰልፍ ወይም በተለያየ መንገድ ለወያኔ/ኢ.ህአድግ ነፍስ ገዳይ ቡድን እንዳትመቹ ጥንቃቄ እንድታደርጉ አጥብቀን ለማሳሰብ እንወዳለን::

ይህ ሰላማዊ ትግል በሃገር ውስጥና በውጭ ሃገር በሚኖሩ ኢትዮጵውያን እንዲሁም ተቃዋሚ የፖለቲካ ሃይሎች በአንድነት « የሃሰት ውንጀላ ያብቃ! የቅንጅት መሪዎችና ሌሎችም የህሊና እስረኞች በአስቸኳይ ይፈቱ!

ብሂራዊ እርቅና የሰላም ጉባኤ በአስቸኳይ ይደረግ!» በሚሉ ወቅታዊ መፈክሮች ስር በሚካሄድ ባለ ዘርፈ ብዙ አለም አቀፍ እንቅስቃሴ ተጀምሮ ቀጥሎአል:: ይህ በውጭ የተጀመረው እንቅስቃሴ ባገር ውስጥም ተጠናክሮ መሪዎቻችን ተፈተው ሕዝባችን የራሱ መጻኢ የፖለቲካ እድል በራሱ መወሰን የሚችልበት ሁኔታ እስከሚፈጠርበት ድረስ በተከታታይ ይቀጥላል:: ሥለዚህ ይህ ሰላማዊ ትግል በታላቅ የፖለቲካ ጥበብና ዘዴ በሚቀየሱ የትግል ሥልቶች ታግዞ ባገዛዙ ላይ ትርጉም ያለው ተጽዕኖ ዕስከሚያሳድር ድረስ ወጣቱና ተማሪው ታላቅ አገራዊ አደራ ተጥሎበታል::

**ከኢትዮጵያ ህዝብ አብራክ ለተገኛችሁት ውድ የአገር መከላከያ፣ የደህንነትና ለፖሊስ አባላት በሙሉ!**

ዛሬ ውድ እናት አገራችን ኢትዮጵያ በመስቀለኛ መንገድ ላይ ትገኛለች:: ይህንን ከመሰለ የፖለቲካ አጣብቂኝ መንጥቆ ለማውጣት ደግሞ ብቸኛው መንገድ አንድና አንድ ብቻ ነው:: የኢትዮጵያን ህዝብ የስልጣን ምንጭነትን መቀበልና ለዕርሱ ፈቃድ እራሰን ማስገዛት ብቻ ነው:: እናንት ያገር ሰላምና ደህንነት ጠባቂ፣ የህግ የበላይነት ዋሰትና፣ የህዝብና ያገር ጥቃት ተከላካይ እንጂ የግለሰብ ሥልጣን ጠባቂዎች አይደላችሁም:: መንግስት በተለወጠ ቁጥር እናንተም አብራችሁ የምትበተኑ ሳትሆኑ ህገ መንግስት ጠባቂ፣ ያገር ደህንነት ዋስትና የህዝብ ልጆች መሆናችሁን አትዘንጉ:: የወያኔ /ኢህዴግ ገዥዎች የስልጣን እድሜያቸውን ለማራዘም በሚስጡት ትዕዛዝ በምትስቡት ቃታ የሚወድቁት ወንድሞቻችሁና እህቶቻችሁ መሆኑን አትዘንጉት:: የምታለቅሰው እናታችሁ ያለጠአሪ የሚቀረው አባታችሁ መሆኑን ምንጊዜም አስቡት:: በተዛባ ፍትህ ያለ አግባብ ዕየተሰቃዩ ያሉ ለሁላችንም ነጻነት የታገሉ የዴሞክራሲና የነጻነት አርበኞች እንጂ አገር ከሃዲ ወንጀለኞች አይደሉም:: ስለዚህ በዚህ ታሪካዊ አጋጣሚ ልናሳስብህ የምንፈልገው ታሪክ የጣለብህን ታሪካዊ ሓላፊነት ተገንዝበህ የትግል መስመርህን በማስተካከል ፍትህ እንዳይዛባ በሀሰት የተከሰሱ መሪዎቻችን፣ የህሊናና ፖለቲካ እስረኞች ካለምንም ቅድመ ሁኔታ ተፈተው ብሂራዊ እርቅ እንዲሰፍንና አገራችን የዜጎች እስር ቤት መሆንዋ እንዲያበቃ የምናካሂደውን ትግል እንድትቀላቀሉ ወገናዊ ጥሪያችንን ዕናቀርባለን::

በመጨረሻም በወያኔ የፈጠራ ክስ በሀገር ክህደት የተከሰሱት መሪዎቻችን፣ የሕዝብ ልሳን የነበሩት ጋዜጠኞቻች፣ የሲቪክ ሀብረተሰብ ታጋዮቻችንና ባጠቃላይ በመላው ኢትዮጵያ በየማጎሪያ ጣቢያው እየተሰቃዩ የሚገኙት የህሊናና የፖለቲካ እስረኞቻችን እስከሚፈቱ ድረስ ትግላችን ይቀጥላል::

በተባበረው ትግላችን ሠርተን የምንኖርባት፣ ወልደን የምንስምባት አንዱ በይ ሌላው ተመልካች ያልሆነባት ፣ በዴሞክራሲ ያበበች፣ በኤኮኖሚ የበለጸገች በዓለም የተከበረች እናት ኢትዮጵያን ለመገንባት እጅ ለእጅ ተያይዘን እንድንታገል ጥሪያችንን እናቀርባለን !

**የተባበረ ትግል ምንጊዜም ያሸንፋል**

**ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ**
**የአለማቀፍ አመራር**